# ህዝበኝነት የህዝብ ጠላትነት!

**ናፍቆት አሰፋ 03-01-18**

የፅሁፌ መነሻ አጩሌ (የአሜሪካው ግቢ ከኢህአዴግ ሜዳ) በኢህአዴግ ሜዳ አውራጅና ጫኝ ለምን በዛ? በሚል ርዕስ ያቀረበው ፅሁፍ ነው። ፀሃፊው የእነሱ ባልሆነው የኢህአዴግ ሜዳ ላይ እንዳሻቸው ሲፈልጡና ሲቆርጡ የሚውሉ የህልም ፈላስፎችን በኢህአዴግ ውስጥ ከተፈጠረው ችግር ጋር አያይዞ አሳይቶናል። ፅሁፉ በውስጥም በውጭም ያለውን ለመዳሰስ የሞከረና የወቅቱን ነባራዊ ሁኔታ በበትክክለኛ ትዝብት በግላጭ ያሳየ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የኢህአዴግ ውስጥስ ምን ይመስል ይሆን በሚለው ላይ አትኩሬ እና በፃሃፊው እይታ ላይ ተመስርቼ ለማየት እሞክራለሁ።

**ህዝብን አለማክበር፣**

የእኛ የፓርላማ አባላት፣ እንደ ሌሊት ወፍ ቀን ቀን አይጥ፣ ሌሊት ሌሊት ወፍ እንሆንም ብለው ለቆሙለት ፕሮግራምና ፕሮግራሙን አምኖ ለመረጣቸው ህዝብ በፅናት በመቆማቸው፣ ነፍሳቸውን ይማረውና የሙታኖቹ ፅንፈኞች መዘባበቻ ሆነዋል። ይሄ የህዝብ ወኪሎቻችን የሆኑት የምክር ቤት አባላት የመጀመሪያ ድል ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ የዴሞክራሲ ማስፋትና ለዴሞክራሲ መስፋት አዕማድ ለሆኑ መሰረቶች እጅግ በብዙ ለመስራት እልህ ሊገቡና መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ እንዲሆኑ የሚያነሳሳቸው ነው። በታሪክ አጋጣሚ የፅንፈኞች የውስልትና ጫናና ማባበያ ለፓርላማችን የመጀመሪያው ነው።

ፓርላማችን የህዝቡ ጥያቄ አገሪቱ ውስጥ እየታየ ካለው እድገት በላቀ ሁኔታና ደረጃ በደረጃ እያደገና እየሰፋ መምጣቱን ተገንዝቦ በተለይ በመልካም አስተዳደር፣ አገልግሎት አሰጣጥና ታላላቅ የመሰረተ ልማት ግንባታ ጉዳዮች አስፈፃሚውን በገለልተኝነት እለት ተዕለት መከታተሉን ባጠናከረበት በዚህ ሰዓት ምክር ቤቱን ለማሳነስ የወሰኑ ፅንፈኞች ሞራል ከሚነካ ትንኮሳቸው ባለፈ ለማስፈራራት ያደረጉት ሙከራ አዋራጅ ነው። የፅንፈኞቹን ስለ ምክር ቤቱ የአሰራር ሂደት ያላቸውን እውቀት አልባነትም ያጋለጠ ነው። ከሁሉ በላይ ደግሞ የደጋፊ፣ የተቃዋሚ ሳይባል የሁሉንም ህዝቦች ጥቅም ለማስጠበቅ የሚሰሩትን የህዝብ ተወካዮች በዚህ ደረጃ መፈረጅ መላውንም ህዝብ በግላጭ የናቀ በመሆኑ በህግ ተጠያቂ መደረግ ያለበት አካል እንዳለም የሚያሳይ ነው።

**የመስመር ተቃርኖ፣**

በአገሪቱ ሰፋ ባሉ አካባቢዎች ለረጅም ጊዜያት ተከስቶ የቆየው የሰላም እጦት በዋናነት በሰላም ወዳዱ ህዝብ፣ በአገር ሽማግሌዎች፣ ወጣቶችና ሴቶች ተሳትፎ እየከሰመና እየበረደ በመጣበት ሰዓት፣ ፅንፈኞቹ አደራጅተው በቀጥታ የሚያሰማሯቸው ሀይሎች በየአካባቢው ህዝብ ላይ የሚያሳድሩትን ጫና ተከታትሎ ለማስቆም መንግስት እንቅስቃሴ ማድረጉ ያሰጋቸው የህዝብ ጠላቶች የፀጥታ መሰናክል ለመሆን ሁሉንም አይነት የጥፋት አማራጭ ለመጠቀም ርብርባቸውን አጠናክረዋል።

ከእነዚህ ውስጥ የኢህአዴግ አካላትን ከቆሙለት ዓላማ ነጥለው የጥፋታቸው አጀቢ እንዲሆኑ የማድረግ እንዲሁም የአባላትን ሚናና ወሳኝነት በማሳነስ የጥፋታቸው የዳር ተመልካች እንዲሆኑ ማድረግ ይጠቀሳል። ከአገሪቱ ሁሉም አካባቢዎች በህዝብ ምርጫ ፓርላማ የገባውንና 547 አባላት ያሉትን የኢፌዴሪ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ህዝብ ሳይመርጠውና የህዝብ ወኪል ሳይሆን ኮሮጆ ሰርቆ የገባ ነው በሚል ያፈጠጠ ውሸት የህዝብንና አገርን ክብር የሚነካ አዋራጅ ተግባር ሲፈፅሙም ታይተዋል።

በኢህአዴግ አባል ድርጅቶች መካከል የሚካሄደውን የሊቀመንበርነት ምርጫ ለተሻለ ተልዕኮ መፈፀምና ቀድሞ ለመሰዋት ከሚደረግ ግምባር ቀደምነት ይልቅ፣ በተንሸዋረረ የዘረኝነት ምልከታና ስዕል አባል ድርጅቶቹ እርስ በእርስ እንዲጠራጠሩና ለብተና እንዲጋበዙ በማድረግ በአገሪቱ መቆሚያ የሌለው አለመረጋጋት እንዲከሰት በከፍተኛ ደረጃ እየተረባረቡ መሆኑ እየታየ ነው።

ይህንኑ የተወላገደና የተንሸዋረረ አስተሳሰብ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ፣ አልፎ አልፎም የድርጅትን መርህ ፊት ለፊት በመፃረርና በመጣስ በተለያየ መልኩ የሚያራምዱ አንዳንድ አመራሮችን እያየን ነው። ጎራ መቀላቀሉ እንዲህ ሰፊ በሆነበትና መስመር ለይቶ በቆመለት ማህበራዊ መሰረትና በራስ የድርጅት አጥር የማይንቀሳቀስ አመራርና አባል እየሰፋ በመጣበት ሁኔታ ችግሮቹ መታየታቸው አስገራሚ ባይሆንም፣ ለኢህአዴግ እና የኢህአዴግ አባል ለሆነ አመራር የማይመጥን ተርታ ህዝበኝነትና የመስመር ጥሰት አለመቆሙ ግን አደገኛ ሁኔታ ላይ እንዳለን ያረጋግጣል።

ህዝባዊነት ድንበር የለውም ብሎ በሚያምነው ኢህአዴግ ውስጥ ተሰልፎ የመንግስትን ስልጣንን የብሄሩ ህዝብ ሳይሆን በብሄሩ ስም ለመነገድ የሚሞክር የኢህአዴግ ሰው በድርጅቱ ታሪክ ታይቶ አያውቅም። የኢህአዴግ መስመር ከሌሎች ተፎካካሪ ወይም ተቃዋሚ ፓርቲዎች መስመር እንደሚለይ የማያውቅ የኢህአዴግ አመራር በድርጅቱ ታሪክ ተሰምቶና ታይቶ አያውቅም።

ቀድሞውኑ ተቃዋሚ ወይም ከኢህአዴግ ጋር ተፎካካሪ የሆነው ፓርቲ የመስመር ልዩነቱን ይዞ፣ የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግስትን አተያይ ተቃርኖና ይህን ተቃርኖውንም በምርጫ ጭምር ሞክሮ በመሸነፉ ተነጥሎ ሳለ እኛና እነሱ ልዩነት የለንም የሚል አስተሳሰብ በእርግጥ የኢህአዴግ ነው ወይ የሚል ጥያቄም ያስነሳል። በእርግጥም ህዝበኝነቱና ጎራ መቀላቀሉ አይሎ እዚህ ደረጃ ከደረሰ ድርጅቱ ራሱን አሁን እያየ ካለውም በላይ በጥልቅ መፈተሽ እንዳለበት ያመላክታል።

**ከየት ወዴት?**

የኢትዮጵያ ህዝብ በትግሉ ያመጣውን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ከመመስረቱ በፊት በብሄሩ ተጨቁኗል። በብሄሩ ተሰዷል። በማንነቱ ተዋርዷል። በዘሩና በአመጣጡ ተሸማቋል። እኩል ሆኖ ለመኖር ስሙን ጭምር ቀይሯል። በቋንቋው ተገፍቷል። በኢኮኖሚ አቅሙ ከተርታም ተርታ ሆኖ ለከፋ ረሃብና ጉስቁልና ተዳርጓል። የኢኮኖሚ መድልኦና መገለልም አሳልፏል። የኢትዮጵያና ኢትዮጵያን የሰሯት ብሄሮች ብሄረሰቦች የረጅም ዘመናት ታሪክ ይህም ጭምር ነው።

የኢትዮጵያ ህዝቦች የመሰረቱት ህገመንግስታዊ ስርዓት በቅድሚያ እነዚህን የጭቆና ገመዶች የበጣጠሰ፣ የራስን በራስ የማስተዳደር ስርዓት ያወጀ፣ ማንም ተጨቁኖ ሊኖር እንደማይችል ዋስትና የሰጠ፣ ለጋራ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ልዩ ትኩረት የሰጠ፣ ለህዝቦች ብልፅግናና ፍትሃዊና እኩል ተጠቃሚነት የቆመ ምርጥ ህገመንግስታዊ ስርዓት ነው።

የኢትዮጵያ ህዝቦች የመሰረቱት ስርዓት ብዙሃን የበላይ፣ ውህዳን የበታች የማይሆኑበት ልዩ የእኩልነት ስርዓትም ነው። ስርዓቱ ብዝሃነትን በቁጥር አይቶ የበላይ እንደማይለው ሁሉ፣ ኢትዮጵያ የብሄር ብሄረሰቦች አገር በመሆኗ በብሄር ብዛት አይቶም አንዱን የበላይ ሌላውን የበታች የማያደርግም ነው፤ ከብሄር አንፃር ትልቁ ኢትዮጵያ 56 ብሄሮች ያሉት ደቡብ ክልል ነውና። ስርዓቱ የቆዳ ስፋትንም አይቶ ትልቁ ክልል ብዙ ጥቅም ማግኘት አለበት አይልም። እንዲያ ቢሆን ኖሮ ትልቁ ክልል የኢትዮጵያ ሶማሌ ነበርና። የስርዓቱ ልዩ ባህሪ እኩልነትን የሚያስተናግድበት ልዩ ሁኔታም ጭምር ነው። ማንም የበላይ፣ ማንም የበታች እንዳይሆን ያደረገ ነው የሚባለውም ለዚህ ነው።

በአንድ በኩል እኩልነቱ ህመም የሆነባቸው በህዝብ ስም ሲነግዱ የኖሩ ገዥዎች፣ በሌላ በኩል የጭቆና ስርዓቱን ንዶ እኩልነቱን ያረጋገጠው መላው ህዝብ መሆኑን ያልተቀበሉ ጠባቦች የኋላ ታሪክ መዝዘው

እንደ ጅብና አህያ ሲበላሉ እንዳልከረሙ ሁሉ ስርዓቱን ሚዛናዊነት አሳጥተው ለማፍረስና ህዝቡን ለብተና ለመዳረግ የእውር ድንብራቸውን ሲንፈራገጡ ይታያሉ።

በግል የወንበርና የስልጣን አተያይ ላይ በነበራቸው ጥልቅ የግል ጥቅም መሻት ቁጭት ላይ ሆነው የእነሱ ከፍታ የህዝቡ ከፍታ እንደሆነ አድርገው በመሳል በብሄርና በማንነት ስም ሲነግዱ ይታያሉ። ታሪክ ራሱን ይደግማል እንዲሉ በጭቁኑ የአማራ ህዝብ ስም ለዘመናት ሲነግድ የኖረው ስዩማዊና መስፍናዊ ስርዓት፣ ይልሰው ይቀምሰው ያልነበረው ጭቁን የአማራ ህዝብ በሌሎች ህዝቦች ዘንድ የስልጣን ባለቤትና ገዥ እንደሆነ አድርጎ ሲያቀርበው ቆይቷል።

በዚህም ምክንያት አማራው እንደ ገዥ መደብ ተቆጥሮ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በተበተነበት አካባቢ ፍዳውን ሲያይ ቆይቷል። አማራው እንደ ሌላው ህዝብ ሁሉ ሲጨቆንና ሲረገጥ እንደቆየ ለማስረዳት የህዝብ ለህዝብ ትውውቁን ማስፋት ባይቻል ኖሮ ቁርሾው በቀላሉ የማይሽር ይሆን እንደነበር የማይካድ ነው።

## የህዝበኝነት በሽታ፣

አሁንም በኢህአዴግ አባል ድርጅት ውስጥ ጭምር ሆነው በህዝብ ስም ስልጣንን የመፈለግ ኢህአዴጋዊ ያልሆነ አባዜ ህዝባዊ ያለመሆኑን ፊት ለፊት መነጋገርና መተማመን ያለባቸው እራሳቸው ኢህአዴጎች ናቸው። ህዝበኝነት የህዝብ ጠላትነት መሆኑን በግልፅ በመተማመን በህዝባዊ አተያይ አብሮ ለመጓዝ በግላጭ መነጋገር ያለባቸው እራሳቸው ኢህአዴጎች ናቸው።

ኢህአዴግ የሚመራው መንግስት በህዝባዊ አተያዩ ድንበር የለሽ መሆኑን ለደቡብ ሱዳን ሰላም መረጋገጥ እዚያው ድረስ ሄዶ ዋጋ እየከፈለና እየሰራ፣ የሶማሊያን ሰላም ለማረጋገጥ በቦታው ተገኝቶ ዋጋ እየከፈለ፣ የጎረቤት አገር ስደተኞችን ከጦርነትና ትርምስ ጠብቆ በአገሩ እየተቀበለና ይህንኑ በተግባር እያረጋገጠ ባለበት በዚህ ወቅት የኢትዮጵያዊነታችን አዕማዶችና ሙላቶች የሆኑት ሁሉም ብሄረሰቦች ያለ አንዳች ስጋት በአገራቸው ሁሉም ቦታዎች መኖርና መስራት ያለመቻላቸው የህዝበኝነቱ መሸርሸር ብቻ ሳይሆን የህዝበኝነቱ በሽታ ያመጣው ነው።

በኢህአዴግ መስመር ላይ መሆኑን የዘነጋ የኢህአዴግ አመራርና አባል አብዮታዊነት ወዴት እያመራ እንደሆነም ማሳያ ነው። ለዚህም ነው በእኛና በተቃዋሚዎቹ መሃል የመስመር ልዩነት የለም የሚል

የኢህአዴግ አባል ተፈጥሮ እያየን ያለነው። በሽታው በመቻቻልና በመከባበር ሳይሆን በመማማርና በመቆራረጥ ሊድን እንደሚገባ በጥልቅ መመካከርም የሚያስፈልገው።

የህዝበኝነቱ በሽታ በቶሎ መዳን ካልቻለና ህመሙ የሚቀጥል ከሆነ በቅድሚያ የሚበላው በሽታው ያለበትንና የሚያስታምመውን አካል መሆኑን መረዳትም እጅግ ወቅታዊ ሆኖ ይታያል። የጅብ ተረት አላብዛና ጅብ የራሱ ቁስል የሌላ እየመሰለው በልቶት ይሞታል እንዲሉ፣ የቆሙበትን ማህበራዊ መሰረት ዘንግቶ፣ ራስን ከማየት ይልቅ በሩቅ ያለን እያሳዩና ችግርን ወደ ውጭ እያደረጉ በስልጣንና መሰል ጥቅሞች ታጥሮ ከዋናው ችግር ጋር የመኖሩ ሂደት ብዙም በህዝብ ውስጥ አያቆይም።

ይልቁንም ይህን እድል በአግባቡ በመጠቀም፣ በህዝባዊ አተያይ መርህ ላይ በመቆም ድህነትን ለማሸነፍ በቀን ከለሊት እሩጫ ለራሱ፣ ለህዝቡ፣ ለአገሩ እድገትና ብልፅግና እየሰራ ያለውን፣ የብልፅግና ተስፋ ያሳየነውን ሁሉንም ህዝብ የሁላችንም አለቃ መሆኑን በተግባር መሪው ሳይሆን ተመሪው ሆነን ብናረጋግጥ መልካም ነው።